# በዕውነት ስለ ዕውነት

የመፅሀፉ ርዕስ- ያሲምባ ፍቅር

ደራሲው - ካህሳይ አብርሃ

ዳሰሳ - ኃይሉ በለሳ

በቅርቡ ለህትመት የበቃውና ትዝታ ቀስቃሽ የሆነውን የአሲምባ ፍቅር የተሰኘውን የካህሳይ አብርሃን መደብል አንብቤ በጣም ተደስቻለሁ። አብሬው ጫካ ለጫካ ከትግራይ ወደ ወሎ ከዚያም ወደ ጎንደር ተንከራተትኩ። የማስታወስ ችሎታውንና ስለ ድርጅቱ ያለውን ዕውቀት አደነቅሁ። ኢህአፓ በሀቡዕ ተመስርቶ ህዝብ የቀሰቀሰ ፤ ያነቃ፤ ያደራጀ ያታገለና የታገለ፤ ዕድሜ፤ ፆታ፤ ዘር፤ ጎሳና ሃይማኖት ሳይለይ የመላ ኢትዮጵያውያንን ቀልብ የሳበ የመደብ ትግልን መሰረት ያደረገ መሪ ድርጅት ሲሆን መደባቸውን ሽጠው የተቀላቀሉትም ጥቂት አልነበሩም። በፕሮግራሙና በልሳኑ በያንዳንዱ ቤት በመግባት የትግል ዘር ዘርቶ የትግል መረብ ዘርግቶና በትግል ፍቅር አስተሳስሮ እንደነ አማኑኤል ያሉ ታጋዮችን አፍርቷል። ባንዳንድ አካባቢዎች በታጠቀው ክንፍ በኢህአሠ ይፋ ሆኖ ለህዝብ ዕይታ ቢበቃም አስፈላጊወን የትግል ዘዴ ዘይዶ የተጠበቀውን የትግል ውጤት አስመዝግቦ ከዳር እስከ ዳር ይደግፈው፤ ይጠብቀውና ይናፍቀው ለነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደተሰየ ቀርቷል።

ከዚህም አልፎ እንኳን ከመላ የኢትዮጵያ ህዝብ አእምሮ ይቅርና ሁሉን ነገር ሰውተው የተቀላቀሉት የድርጅቱ አባላት ዕውነውተኛ የትግል ሂደቱንና ታሪኩን በትክክል ጥርት ባለ አኳኋን ሳያውቁት በትግሉ ሂደት ወድቀው ከተቀበሩት ጋር ተቀብሮ፤ ከታሰሩት ጋር ታስሮ፤ ከቆሰሉት ጋር ቆስሎና ከተበተኑት ጋር ተበትኖ መቅረቱ የብዙዎችን ህሊና ሲከነክን አርባ ዓመታት እያስቆጠረ ነው። ምስጋና ይግባውና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በየ አቅጣጫው ታሪካችን ከተቀበረበት እየተቆፈረ፤ ከተበተነበት እየተሰበሰበና የተቆራረጠው እየተቀጠለ ብቅ ብቅ ማለቱ ከብዙ የተናጠል ጥረቶች በኋላ የተሟላ ታሪኩ አንድ ቀን ለህዝብ ፀሀይና ጆሮ የሚቀርብ ለመሆኑ የአሲምባ ፍቅር አንድ ምስክር ነው።

የኢህአፓ/ኢህአሠ የትግል ታሪክ በሚነገርበት ጊዜ አንድ ሊለመድ የሚገባውና አደራ የሚባለው ቁም ነገር “ዕውነት” ነው። በከተማም ይሁን በገጠር ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ታሪካችን በዕውነት ስለዕውነት ቀርቦ አገር ያንጓልለው። ለሰሚው እንዲጥም፤ ጠላት እንዳይጠቀምበት፤ እንዳይተች፤ ከሚል ወይም የሚወዱትን ማር የሚጠሉትን ዕሬት ቀብቶ አንዱን ወንጅሎ ሌላውን ተከላክሎ፤ አንዱን ኢጋንኖ ሌላውን አንኳሦ፤ ከዶ ወይንም ደብቆ፤ ሳይሆን ዕውነተኛ ታሪኩ በተደረገበት መልኩ የማስታወስ ችሎታ እስከፈቀደ ድረስ በትክክልና ግልፅ በሆነ በማያሻማ ሁኔታ ቢቀርብ መማሪያ ይሆናልና በዕውነት ስለዕውነት እንናገር።

ከአማኑኤል መልካም ትዝታዎችና ጠቃሚ ትምህርቶች ከማግኘቴ በበለጠ የሚቀጥለውን ታሪክ ፀሀፊ “ማነህ ባለሳምንት” ብሎ ስለሚያነቃቃ ከመቀመጫየ አፈፍ በማለት አመስግኘዋለሁ። እኔም በዚያ የትግል ማዕበል ውስጥ ስላለፍኩ በተመስጦ ነበር መፅሀፉን ያነበብኩት። የታሪኩ ባለቤት እንደመሆኔ መጠን የኢህአፓ/ ኢህአሠ ስም ሲነሳ መላው ሰውነቴ አብሮ ይነሳል። የተነሳው በጥሩ ከሆነ መንፈሴ ይፈነድቃል። በመጥፎ ከሆነ ግን ከቁጥጥሬ ውጭ በሆነ መንገድ ፀጉሬ ይቆማል። ቆዳየ ይኮፋተራል፤ የውስጥ የሰውነቴ ክፍሎች ሳይቀሩ ይቆጣሉ። ስሜቴ ይጎዳል። እኔ ራሴ ግን ኢህአፓ/ ኢህአሠን በመጥፎ ባነሳው ምንም አይሰማኝም። ለለምን? የኔ ስለሆነ። በተለይም ድርጅቱን የማያውቁት ሰዎች ባገኟት ቁራጭ ወሬ ተመርኩዘው ሙሉ ፍርድ ሲፈርዱበት ነው ፀጉሬ የሚቆመው።

የሚጠሉትና የሚፈሩትም የባሰ እንጂ ያነሰ ውንጀላ ስለማያቀርቡበት ከፉኛ ያንገበግበኛል። ይህን ስል ድክመቴን ለመግለፅ እንጂ ኢህአፓ የሁሉም ጭቁን ኢትዮጵያውያን ወኪል፤ ኢህአሠ ደግሞ ሙብት አስጠባቂ ቀይ ሠራዊታቸው በመሆኑ ማንም ያገባኛል የሚል የህብረተሰብ ክፍል ሁሉ ሊያወሳው ይገባል። ብዙዎች የጥላቻ ስሜት የሚያዘወትሩትም የመጨረሻውና ዕውነተኛ ተስፋቸው ኢህአፓ ስለነበር ያንን የነፃነት ተስፋ ዕውን ባለማድረጉ እንጂ ሌላ ጥላቻ ኖሯቸው አይደለም። ስለዚህ በዕውነት ስለ ዕውነት ጥንካሬውና ድክመቱ፤ ትክክለኛ ግፅታው ቁልጭ ብሎ ቢወጣ በታሪክ መዝገብ ተመዝግቦም በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሌላ አገር የሚገኙ ጭቁን ህዝቦች ለሙብት ፤ ለነፃነት ፤ ለእድገትና ለብልፅግና ሲታገሉ የሚማሩበት ሀቅ ሆኖ ይቀመጣል።

ወደ ተነሳሁበት ቁምነገር ልመለስና ዕውነትም አማኑኤል ለአሲምባ ይኸ ነው የማይባል ፍቅር ነበረው። ይህንንም ፍቅሩን ከ5-250 ባሉት ገፆች ጠቅሶታል። ያ ፍቅር ደግሞ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ሕዝባዊ፤ አገራዊ፤ ጓዳዊና አሲምባዊ ፍቅር ነበር። ይህን ፍቅር ነው አማኑኤል በነዚህ ገፆች የሚነግረን። ዕውነተኛ ፍቅር በመሆኑም ከዚያ የሕዝብና የትግል ፍቅር አማኑኤልን ርሃብ፤ ጥማት፤ መውደቅና መነሳት፤ የደርግ ሃይል፤ መድማትና መሞትን ጨምሮ ከዓላማው ንቅንቅ አላደርጉትም። ጓዶቹ ከፊቱ እየወደቁ ሞትን በዓይኑ እያየ ባዶነት ተሰምቶት ከወሎ አሲምባ መልሶ የወሰደው ያ ፍቅር ነበር። በፊት ወደነበረበት የትግል ጥንካሬ ሊመልሰው የሚችለው ከሌሎች ጓዶች ጋር የነበረው ሕዝባዊና ጓዳዊ የአሲምባ ፍቅር መሆኑን አውቆ ብቻውን ያን ሁሉ ጉዞ ተጉዞ ኢህአሠን የተቀላቀለው። የአማኑኤል ያሲምባ ፍቅር ዕውነተኛ የሕዝብ ፍቅር በመሆኑ ይመር ንጉሴን እንኳ በዚያች ቅፅበት የተመጣጠነ ሕዝባዊ ወገናዊ ፍርድ ፈርዶለታል( ገፅ127)። የዕውነት ለመናገር ከሆነ እኔ ብሆን ይመር ንጉሴን አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁለት ሶስት ጊዜ እንኳ ብገድለው የወደቁትን ጓዶች ደም በብቃት አይመልስም። ደግነቱ ፈራጁ እኔ ሳልሆን አማኑኤል ነው።

አማኑኤል በዝርዝር የተነተናቸውን የጫካ ውስጥ መንገዶች፤ የገጠር ከተሞች፤ መንደሮች፤ የሰው ስሞች ስብሰባዎችና ጦርነቶች ከታሪኩ ባለቤት ውጭ ለሆነው አንባቢ እንደሚሰለችና የመጽሓፉ ተነባቢነት ውጤት አልባ እንደሚሆን የተገነዘበው አማኑኤል ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ሊያሳትፍ የሚችል ጊዜ የማይሽረው ሁለንተናዊ ባህሪይ መጨመር አስፈልጎታል። ይህ ሁለንተናዊ ባህሪይ በቆንጆት "ምርኮኛ" ላይ ተመርኩዞ የፍቅር ፅንሰ ሀሳብ የተጨመረበት ይመስላል። ይህ ፍቅር ከአሲምባ ፍቅር የስም አንድነት ይኑረው እንጂ በይዘቱ የተለየ በሁለት ተቃራኒ ፆታዎች መካከል የሚተገበርና ዓለም በሙሉ ገብሮለትና ሰግዶለት የሚኖር ክስተት ነው። ስለዚህም አማኑኤል ከዚያ ትውልድ በተጨማሪ ይህን ትውልድ አብሮ የሚያሳፍር ሰፊ ጠንካራ የፍቅር መርከብ ፈልጎ ድላይን አገኘ (ገፅ 250)። ይህን ስል ግን አማኑኤል ድላይን አያውቃትም ወይም አይውዳትም ለማለት ፈልጌ አይደለም። እውነቱን እርሱ እንደሚወዳትና እንደሚያፈቅራት ምፃፍ እንጂ መፅሃፉን ተነባቢ ለማድረግ ሲል ከህዝባዊና ጓዳዊ ፍቅር ውጭ ጾታዊ ፍቅር እንደነበራቸው መጻፍ አልነበረበትም። ከዚህ ድምዳሜ ላይ ብቻየን ብደርስም ግን እንደ እኔ ድላይን የሚአውቋትን ሳነጋግር በጉዳዩ ከኔ በበለጠ እንደተበሳጩ ተረድቻለሁ። ድላይን እንደ አማኑኤል እኔም አውቃታለሁ። እወዳታለሁ። ሳውቃትና ስወዳት ግን በጓዳዊና በህዝባዊ ግንኙነት እንጂ እንደ እርሱ በሌላኛው የፍቅር መልክ አይደለም። ሌሎቹ ጓዶችም እንዲሁ።

ድላይ ለውንዶች ጓዶች ይሁን ለሴቶች ጥሩ የታጋይ አርአያ ነበረች። አማኑኤል እንደሚገልጻት ግን ድላይ መልከመልካም፤ ፀጉረ ሉጫና እንከን የሌላት ቆንጆየ ሳትሆን (ገጽ 433) የወታደራዊ ቁመናዋ ከትጥቋ ጋር አብሯት የተፈጠረ የምትመስል የህዝባዊ ሠራዊት ተክለ ሰውነት የነበራት ተጋዳይ ነበረች። ፀጉሯንም ለመሸፈን አዘውትራ ኮፍያ ትለብስ ነበር። ፀጉሯ ሉጫ አለመሆኑ የድላይን ጓዳዊ ፍቅር አይቀንሰውም። ድላይ ለጠላት ቆራጥ የነበረችውን ያክል ለውገን ደግሞ አንደበት ለሌለው አንደበት፤ መብቱን ለተነጥቀው የመብት ጠበቃ፤ አቅም ላነሰው መካች ክንድ፤ ወኔ ለከዳው የጀግንነት ካባ የምትደርብ (ገጽ 296) የጀግና ጀግና የኢህአሠ ተዋጊና አዋጊ አርበኛ ነበረች።

የድላይ መልከመልካምነትና ሩህ ሩህነት የራሷን ጥቅም ሰውታ የጓዶቿንና የቆመችለትን ምዝብር ህዝብ ጥቅም ታስቀድም ነበር። የቁመናዋን ማማር ለማያውቁት አስምሬ ለመግለጽ ቃላት ባይኖረኝም የፊልድ ጃኬቷን፤ ገንባሌዋንና ኮፍያዋን አድርጋ ከበስተኋላዋ ለሚያያት ወንድ እንጂ እሴት ነች ብሎ የሚጠረጠር አይኖርም (ገፅ302) ነበር። አንድ ጊዜ ሃይል 23 ውስጥ በነበርንበት ወቅት ቀስቃሽ ትይንት ( theater) አብረን ስንሰራ እኔና ጓድ ለገሰ በድምፅ እየተቀባበልን ታሪኩን ስንናገር (narrate) ድላይና ሊሎች ጓዶች ተግባሩን ያሳዩ ነበር። በትይንቱ አብሪ የነበረው ጓድ በእንዝህላልነት እየመራ ወስዶ ከጠላት የጦር ሰፈር ይጥላቸዋል። በተፈጠረው ሁኔታ ተኩስ ይጀመራና በውጊያው መሃል ድላይ ትሞታለች። ትይንቱም በዚህ ይዘጋና ድላይም ትነሳለች። ትይንቱን ይመለከቱ ከነበሩት መሃል አንድ አዛውንት በትካዜ " ይህን ቁንጅናና ቁመና አፈር ትመኙለት? ነውር አይደለም እንዴ?" ሲሉ የተቆጡት ትውስ ይለኛል።

ለአማኑኤል ተጋድሎአዊ ውሎ ያለኝ አድናቆትና ክብር ከፍ ያለ ነው። በሌላ በኩልም ማንም ተራ ወንድ ድላይን አይቶ ለወሲብ ወይም ለትዳር አለያም ለፍቅረኛነት የማይመኝ ወንድ ልጅ አይኖርም። ድላይም ጾታዊ ፍቅሯን በህዝብዝዊና በጓዳዊ ፍቅር ተክታው እንጂ የርሷም ተፈጥሮአዊ ፍላጎት መኖሩን አልዘነጋውም። እንደማንኛውም ስጋ ለባሽ ፍጡር በስህተት የወሲብ ግንኙነት ቢኖራትም አይደንቀኝም። የኔም ሆነ የሌሎች አግራሞት ግን የድርጅቱን ስነሥርዓት ወደ ጎን ገፍቶ(ጥሶ) ትግሉን በሚያናጋ መልኩ ታስቦ፤ ተውጠንጥኖ፤ ተመክሮና ተዘክሮ ከድል በኋላ ለሚኖር ህይዎት ከአማኑኤል ጋር የገባችው የፍቅር ቃልኪዳን ( ገፅ 299) የድላይ ባህሪይ ሆኖ መፃፉ የሚታለም ብሎም የሚታመን አይደለም።

ድላይ የትግል ስሟን ስታወጣ አብሪያት ባልኖርም በበለሳ የኢህአሠ ቆይታችን ከጋንታ መሪነት እስከ ሃይል መሪነቷ ሳውቃት ከድል በኋላ ለመኖር ፍላጎቷን የሚያንፀባርቅ አንድም ምልከት አላየሁም። ያየሁት በድፍረት በጦዘው ጦርነት መሃል እየተራመደች ስታዋጋ ጥይት እንደሚተኮስ እንኳ ልብ የምትል አትመስልም። ድላይን ሳውቃት እስትንፋሷ እስከምትወጣ ድረስ ህይዎቷ ለትግሉ እንጂ ከድል በኋላ ለሚኖር ህይዎት አልነበረም። ትግሉ የሚጠይቀውን መሰዋዕትነት ከፍላ በደምና አጥንቷ ህዝባዊ ሥርዓት ለማንፅ የቆረጠች የትግል መሃንዲስ እንጂ እርሷም ሆነ ሌላ ሰው ከድል በኋላ የሚኖር ህይዎት ታይቷት አያውቅም። ድላይ ማለት፡-

ሀ- ከድል ላይ ሆኘ (on victory)

ለ- ድልን ለማየት (to see victory)

የሚል ትርጉሞችን ያካተተ የትግል ስም እንደነበራትም የተረዳሁት በተሰዋችበት ወቅት ጓድ ይትባረክ (ቦግን) የአሁኑ ህላዌ ዮሴፍ በገጠመላት ግጥም ነበር። ድላይ በግብር ሲበዛ ደፋር፤ ቆራጥ፤ ፈጣን፤ ጀግና፤ ህይዎቷ የሚቀጥለውን የጥይት ወላፈን ለመቅመስ በጉጉት የሚጠብቅ፤ በአጽሟ ለሚገነባው ድልድይ የወከለችው ሰፊው ህዝብ ተሻግሮ ከድል እንዲደርስ የታገለችና ያታገለች የህዝብ ልጅ ነበረች።

አንድ የማይካድ ሀቅ ግን የድላይ ብቻ ሳይሆን የብዙዎቹ አዋጊዎች ችግር ነበር። አዋጊዎቹ ከማዋጋት ተዋጊ ይሆኑ ነበር። በምንም መልኩ ይሁን ለራስ ጥንቃቄ የሚባል አያውቁም። አንድ ጓድ መሪ የሚሆንበት ምክኒያት ከመስራቱ ማሰራቱ የበለጠ ውጤት እንደሚያመጣ ታምኖበት ነበር። ድላይ በጦርነት ላይ የተዋጊዎቹ የውጊያ ሁኔታ ካልጣማት አጠገቧ ካለው ጓድ መሳሪያ ነጥቃ ነበር ራሷ የምትገባበት። መሪ ወይንም አዋጊ የጦርነቱን ስኬታማነት መለካት ያለበት ራሱን ጠብቆ ከወዲያ ወዲህ እየተንቀሳቀሰ የተሰጠውን ቀጠና እየገመገመ ማዋጋት ሲችልና ወደ ጠላትም ሲጠጋ በከባድ የተኩስ ሽፋን የጠላትን አንገት አስቀብሮ የሚመራውን የጦር ክፍል ለጨበጣ ውጊያ ወይንም ለወረራ ማብቃት ነው። ድላይ ግን (ገጽ120) አንገቷን እንኳን ዘንበል ማድረግ አታውቅም። በወቅቱ ድርጊቷን "አጉል ጀብደኝነት" እንለው ነበር።ያ ሁሉ ጀግንነት አስተማሪነቱም ወቅታዊነቱም አሁን አልፏል። ደግሞስ የኔን ሞት ሙታ እኔን በህይዎት እንድቆይ እድል ለሰጠችኝ ሰማዕት ራሷን መከላከል በማትችልበት ሁኔታ ይህን ትችት ልተቻት ከቶውን እንዴት ይቻለኛል?

ከድላይ ጋር በተሳተፍኩባቸው ጦርነቶች ሁሉ በህይዎት ቆይቶ የትግሉን ፍሬ ለመብላት የመፈለግ፤ አግብቶና ወልዶ የመኖር ፍላጎት የወለደው ፍርሃት አይቼ አላውቅም። በዳሞት ጦርነት ላይ የነበረውን ሁኔታ ላካፍላችሁ። ከቆላማው የበለሳ ግዛት ጎለጌ ወንዝን ከተሻገርን በኋላ ከደጋው መሬት ዳሞት እስከንደርስ ውሽንፍር(ነፋስ የበዛበት ዝናብ) ያጣድፈን ጀመር። የለበስነው ልብስ ለቆላ እንጂ ለደጋ የሚሆን ስላልነበር እጃችን ደነዘዘ። ጥርሳችን እርስ በራሱ ይፋጭ ነበር። ሰውነታችን እንደ ባህር ላይ ቀጤማ ይንገደገድ ነበር። የመሳሪያችንን ቃታ ለመሳብ ተቸገርን። ወደ ማጥቂያ ወርዳው ስንጠጋ በጥናቱ ላይ ያልነበረ እሾሃማ የሽቦ አጥር ገጠመን። ከአጥሩ ውስጥም የድልድይ መስሪያ ትልልቅ የስሚንቶ ቱቦዎች ተደርድረው የደርግ ወታደር በቱቦዎቹ ራሱን ከልሎ ይከላከለን ነበር። በዚህ ሁኔታ ነበር ድላይ የሽቦውን አጥር ወደላይ ከመሬት አንስታ በስሩ እየሾለክን ወደ ውስጥ እንድንገባ በስም እየጠራች አንተ ያን ቦታ ቶሎ ተቆጣጠር፤ አንቺና አንተ ይህን ስፍራ ቶሎ ያዙ፤ እገሌ ወድዚያ ጠላት ቦምብ ወርውር፤ . . .ወዘተ ስትል ጠላት ይሰማት ነበር። ድላይ ግን ዒላማ እሆናለሁ የሚል ህልም አልነበራትም። በዚህ መንገድ ሁላችንም ወደ ደርጉ ምሽግ እንደገባን ጓድ ገብረህይዎት አጠገቧ ተሰዋ። የርሱን አኤዋን አንስታ እንደ ማንኛችንም ትዋጋ ጀመር። የሌሊቱ ወረራ እርሷ ትመራው በነበርው ክፍል ስኬታማ ሆነ።

ድላይን እኔ ሳውቃት እንዲህ የጦር ፊታውራሪ እንጂ በመሓፉ እንደ ተቀረጸችው የጾታ ፍቅር አሳዳጅ አልነበረችም። ጓዲት ሴቶችም ሆኑ ውንዶች በክብር ይመለከቷት ስለነበር እርሷም የአርያነት ግብሯን ዝቅ ያደረገችበት ጊዜ አልነበረም። በተለይም ሴት ጓዲቶች እርሷን መሆን ስለሚሹ አዘውትረው ከድላይ ጋር መወያየትን ይመርጡ ነበር። በምጨርሻው እንቅስቃሴያችን በበለሳ ድርጅቱ ለመፍረስ ቀን እይቆጠረና ብዙው ተጋዳይ ወደ ደርግ ይገባ በነበረበት ወቅት " አይዟችሁ ተረጋጉ በማለት በትግሉ ውስጥ እንዲቆዩ ታበረታታ ነበር። ሆኖም መሄድ የሚፈልጉትንም ሴት ጓዲቶች ልትሄዱ ስትቆርጡ አማክሩኝ በጾታችሁ መንገድ ላይ ከሚደርስባችሁ ጥቃት የምትከላከሉበት መሳሪያ እሰጣችኋለሁ" ትላቸው እንደነበር በጊዜው የሴቶች ኮሚቴ አመራር የነበረችው ጓዲት አበባ አላዛር አጫውታኛለች።

አማኑኤልና ድላይ አሲምባ በነበሩበት ወቅትም አንዳንድ ምሁራን ነን የሚሉ ጓዶች ያሳዩ በነበረው የንቀት ስሜት የአንዳንድ ጓዶችን የትግል ስሜት ይጎዱ ስለነበር ድርጅቱን በመልቀቅ ወደየመጡበት ከድተው ይሄዱ ስለነበር (ገጽ312-314) ድንቅየ ተዋጊ የነበረውን አማኑኤልን “ሳታማክረኝ እንዳትሄድ” (ገጽ 287) እንደምትለው አልጠራጠርም። ያ ግን አበረን ከድተን ትዳር መስርተን ፍቅርን ያለገደብና ያለ ተፅእኖ እንኮመኩማለን ማለቷ እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ። አማኑኤልም እንደሚነግረን ዕውነት የፍቅር ቃል ኪዳን ቢኖራቸው ኖሮ ድርጅቱን ለቆ ሲሄድ የሰፈሩን ልጆች አፈላልጎ (ገጽ 392-395) ከነርሱ ጋር ተመካክሮ ከመሄድ ወደ “እጮኛው” ወደ ድላይ በሄደ ነበር። በመጨረሻም ያ ሁሉ ውጣ ውርድ አልፎ የድላይ ፍቅር ወደ ሱዳን ብሎም ወደ አሜሪካ አብሮት ተሰዶ ሌላ ሰው በቅጡ እንዳያፈቅር እየከለከለው በነበረበት ሁኔታ አገር ቤት ሲሄድ ነብሴን አዳነኝ የሚለውን ይመር ንጉሤን ወሎ ድረስ ተጉዞ ፈልጎ ሚስቱንና ልጆቹን እረድቶ ሲመለስ የድላይን ቤተሰቦች ግን ሳያይ ነበር የተመለሰው። ለአማኑኤል ከይመር ቤት ይልቅ የድላይ ቤተሰቦች ቤት ለመንገዱ ይቀርብ ነበር። ወደ ጎንደርም ጎራ ብሎ ከድላይ መቃብር ላይ አበባ አስቀምጦ መመለስ ይችል ነበር። የሆነው ሆኖ  ድላይ በመጽሃፉ ውስጥ የገባችው እንዳናባቢ ለመጽሃፉ ማጣፈጫ እንጅ እውነተኛ ፍቅረኛው መሆኗ ውሃ የሚቋጥር ዕውነትነት የለውም። አለያማ አማኑኤል በለሳ ሄዶ ከመቃብሯ ራስጌ ቆሞ ወታደራዊ ሰላምታ በመስጠት እርሙን አውጥቶ መመለስ ይችል ነበር። የድላይ በመጽሃፉ መግባት ማናበቢያና የመጽሃፍ ማሻሻጫ እንጂ የአማኑኤል “እጮኛ” የፍቅር ቃል ኪዳን በመሆን አይደለም። ሌላም እውነትነት የጎደለው ነገር በመጽሃፉ አይቻለሁ። እስከ 2005 መጨረሻ ድረስ በለሳ ውስጥ ድላይ ተራራ( ገጽ 436) የሚል በስሟ የተሰየመ አንድም ተራራ የለም። ዳዊት ተራራም እንዲሁ። ያለው ገደይ ተራራ ነው። አጭቃን ተራራ ብቻ ነው በለሳ ውስጥ በጓድ ግደይ ጅብዱ የተሰየመ። ይህን ሀቅ የመጀመሪያ ልጁን ድላይ ብሎ ከሰየመው ከአድናቂዋ ከዮናስ በለሳ ሃሙሲት ድረስ ሆዶ አረጋግጦልኛል።

አማኑኤል ከድላይ ጋር አለኝ የሚለው ፍቅር የማናበቢያና የማሻሻጫ ቅመም እንጂ እውንነት የነበረው ፍቅር አይደለም። አማኑኤል አንድ ጊዜ ጠንከር ብሎ ወደ ድላይ ከንፈር ሲጠጋ (ገጽ298) “አንተ ልጅ አታርፍም አለችኝ” ይላል። ከዚህ የጠነከረ ነገር በዚያን ወቅት ለአማኑኤል ቢነገረው ድርጅቱን ለቆ ሊሄድ ይችል ነበር። ድላይ ግን ሰውን እንደንቃተ ህሊናው ተይዝ ስለነበር ከድርጅት ጠቀሜታ አንጻር ድንቅየ ተዋጊ የነበረውን አማኑኤልን ላለማስበርገግ ጥንቃቄ አድርጋ ነበር የገስጸችው። የድላይ ህዝባዊነትና ጓዳዊ ፍቅር የኔን ምስክርነት አይሻም። አስዛኙ ነገር ግን በአለቀ ሰዓት ድርጅቱ እየፈረሰ በነበረበት ወቅት፤ ተጋዳዩ ወኔው በቀዘቀዘበትና ሞራሉ በወደቀበት ሰዓት ከርቀት በተተኮሰ የሚልሻ ጥይት ተመትታ የስርዓቱን እድፍ በደሟ ልታጥብ ከፍተኛውን መስ ዕዋዕትነት በህይዎቷ ከፍላ ለሀገሯ፤ ለወገኗና ለጓዶቿ ደህንነት ራሷን ሰጥታለች። ድላይ የአማኑኤልን የፍቅር ቃል ኪዳን ጠብቃ በወሎ በኩል ትግራይ ሄዳ ስታጣው ወደ ሱዳን ከዚያም ወደ አሜሪካ አልመጣችም።

ታሪክ በምንጽፍበት ጊዜ በዕውነት ስለዕውነት የሆነውን እንጂ የየግል ፍላጎታችንን በሚያረካ መልኩ መጣመም የለበትም። በተለይም እንደነ ድላይ በህይዎት በሌሉ ሰዎች አወንታዊም ይሁን አሉታዊ ምስክርነት ሊሰጡ ወይንም ራሳቸውን ሊከላከሉ በማችሉ ሰማዕታት ታሪክ ላይ ጭቃ መቀባት የታጋይ አፅም እንዳይወቅሰን ይሉኝታ ሊኖረን ይገባል። ድላይ የፍቅርን ጣዕም ገና በከተማ እያለች አጣጥማ የጨረሰች መሆኗን ከአድማስ ባሻገር እንለው በነበረው የኩሽክ ዋርድያ ጊዜ ታጫውተን ነበር። ከሁሉም በላይ ግን ድላይ ኢህአፓ/ኢህአሠን ስትቀላቀል የፍቅር መሸመቻ ገበያ ወሎ ውስጥ አጥታ አሲምባ ውስጥ አገኝዋለሁ ብላ አልነበረም።

የሆነው ሆኖ ግን ያሲምባ ፍቅር መነበብ ያለበት መጽሀፍ ነው። አማኑኤል ስለ ድላይ ከሰነቀረው “ታሪክ” ውጭ የነበረው ፍቅር የህዝብ፤ የጓዳዊ፤ የአሲምባና የአብዮታዊ በራሱ የተሟላ ፍቅር ነበር። አንዳንዶች እንደሚሉትም ለምን ከሰላሳ ዓመት በኋላ? አይባልም። ለምን ቢባል ታሪክም የራሱ ህይዎት አለውና ጊዜ አይሽረውም። ጊዜውን ጠብቆ ሁኔታው ሲፈቅድለት ይንገራል እንጂ አንድንዶች በፈለጉት ሰዓት ካልተጻፈ ታሪክ አያሰኘውም  አይባልም። የግል ኑሮን አቸንፎ ከሰላሳ ዓመት በኋላታሪክን  መጻፍ በራሱ ያስመሰግናል እንጂ አያስወቅስም።

ታሪክን ታሪክ የሚያደርገው እውነትነቱ፤ አስተምሮነቱ፤ ሳይቀነስና ሳይጋነን በማያሻማ መልኩ መነገሩ ስለሆነ በተፈጠረበት፤ በተሰራበት ሁኔታ ዕውነት ስለ ዕውነት በዕውነትነቱ መነገር ይኖርበታል።

እኔም እንደ ሰዎች ዕውነትን እሻለሁ

ዕውነት ተናገሩ በዕውነት ጻፉ ሳለሁ

እውነት ዳተኛ ነች እኔ እቀድማታለሁ

እንዲሉ ነው ይህ ጽሁፍ በራሴና በበለሳ ጓዶች በህይዎት ባሉና በህይዎት በሌሉ ስም የተጻፈው። ሆኖም ሃሳቡ እኔን አይወክለኝም የሚሉትን ጓዶች መብት አከብራለሁ።

ኃይሉ በለሳ abirhanu@bellsouth.net

ጳጉሜ 2005